# የታላቁ ኢትዮጵያዊ የስነፅሑፍና የፍልስፍና ሰው የኃይሉ ገብረዮሐንስ (ገሞራው) ዕለተ ትንሣዔ

ከስቶክሆልም የተላከ

ለዚህ ፅሑፍ ዕለተ ትንሣኤ! የሚል ርዕስ መስጠት የፈለግሁት ካለምክንያት አይደለም። አንድ ቀን ኃይሉን ለመጠየቅ ቤቱ ሄጄ፣ "እንደምን ሰንብተሃል? ጤንነትህስ እንዴት ነው?" ስለው ከሰጠኝ መልስ በመነሳት ነው። "ደህና ነኝ! ሰው እኮ በህይወት እስካለ የሚቻለውን መልካም የሆነን ነገር ሁሉ እያረገ ከኖረ፣ ሞት መፈራት የለበትም፣ ይህማ ህልፈተ ሥጋ ነው። ትንሣዔውማ ገና ነው። በሥጋ ካለፈ በኋላም የሚቀጥል እስከዚያ እለትም ብዙ የሚያደክም፣ የድምር ሂሳብ መክፈያ፣ የሥራና የተግባር ውጤት ነው" አለኝ። አልገባኝም አብራራልኝ ብለውም፣ ያ ሁሌ ፊቴ ድቅን የሚለውን ፈገግታውን እያሳየኝ፣ አማርኛውን ከግዕዝ እያቆላለፈና እያስተሳሰረ ስላከበደብኝ፣ ይህን መሰል ውስጠ ወይራ ጣዕም ያለውን ጨዋታውን አቋርጬው ሌላ ጨዋታ ውስጥ ገባን።

አዎ! ኃይሉ ገብረዮሐንስ ማን እንደሆነ ምስክር አያሻውም። ሥራው፣ ፅናቱ፣ አልበገሬነቱ ፣ ለዘረኞችና ለፋሽሽቶች፣ ለበዝባዦችና ለጨቋኞች አልገዛም ማለቱ፣ እንዲሁም ፍፁም ሰብዓዊነቱ ቋሚ ምስክሮች ናቸው። ከዚህ በመነሳት ነው፣ ዛሬም ኃይሉ ሕያው ነው የምንለው። ዛሬም ገሞራው ይሰማናል። የሱን እምነት የህዝብና የሃገር ፍቅር እስከተላበስን፣ የሀገርና የህዝብ ፍቅርን ለባዕዳንና ለዘረኛው ወያኔ አሳልፈን እስካልሰጠን፣ ለርካሽ ጥቅምና ትርፍራፊ ካልተገዛን። ጋሼ ኃይሉ! ስማኝ አዳምጠኝ፡-

አንተን ባየሁበት ሌሎቹን ሳያቸው፣

ትንሽ ይመስሉኛል ነብስ ያልዘራባቸው።

መሬቱን ሲያርሱብን አየን ዝም ብለን፣

ሲሸጡት ሲገዙት ህሊናንም ጥለን፣

አንተ ግን!

መልሱን ሰጥተኸን ነበረ፣ ለዚህም ማርከሻ!

"ዘር ሳይዙ መሬት ምን ያደርጋል ብለህ

ተደራጅቶ መቆም፣ ዘር ማፍራት ነው ቅድሚያው የቤቱ ማደሻ"

ብለህ ለኛ ነግረህ።

ዛሬ ይህ ፅሑፍ በሚቀርብበት ወቅት፣ የገሞራውን አስከሬን ለዘረኛው ፀረ መብትና ፀረ ኢትዮጵያው ወያኔ ለመሸጥና፣ ሥራዎቹንም እጅ መንሻ ለማድረግና ከወያኔ ጥቅም ለማግኘት ከፍተኛ አስረሽ ምችውና ርብርቦሽ እየተካሄደ ባለበት ወቅት ነው። የምፃት ወቅት ነው ማለትም ይቻላል።

የዚህ ፅሁፍ ዋነኛ ፍላጐት በዚህ ተግባር የተሰማሩትን ግለሰቦች በነቂስ ከቀደምት ታሪካቸው ጭምር በማውጣት በቅድሚያ ለኢትዮጵያ ሕዝብ፣ በማስከተልም በውጭ አገር ነዋሪ ለሆነው ዜጋ እንዲያውቃቸው ለማድረግ ነው። ወያኔ የኢትዮጵያን ሕዝብ እያሰቃየ እየገዛ ስላለ፣ ታጋይ ኃይሎችና የኃይሉ ገሞራው መልዕክትና ዓላማ ተከታዮች ኢትዮጵያን ለቀዋል ማለት አለመሆኑን እንዲያውቁትም ለማሳሰብ ነው። የካቲት አይደገምም፣ ወያኔም ቋሚ ነው የሚል ምድራዊም ሆነ ተፈጥሮዓዊ ህግ የለም። ሕዝብ እየተሰቃየ ባለበት ቦታ ሁሉ የአመፅ ገሞራ መፈንዳቱ አይቀሬ ነው። በ66 የየካቲት አመፅ ከህዝባችን ጋር ነበርን፣ ዛሬም አለን። በየካቲቱ ሕዝባዊ አመፅ ወቅት በፋሽሽቱ መዋቅሮች ውስጥ ገብተን ሰርተናል፣ የህይወት መስዋዕትነት የከፈሉም የህዝብ ልጆች አፍርተናል። በወያኔም መዋቅር ውስጥም ተመሳሳይ ክንውን አያደርጉም ብላችሁ ካሰባችሁ ከሃዲና ደናቆርትም ናችሁ ማለት ይቻላል። “ጠላትማ ምንጊዜም ጠላት ነው፣ አስቀድሞ መግደል አሽኩሻኪውን ነው።” የሚባልም አባባል አለ፣ ይህንንም ትኩረት ውስጥ ብታስገቡት ጥሩ ነው። ከኢትዮጵያ ሕዝብ ከተለያያችሁ ቆይታችኋል፣ ከወያኔም በፍራቻችሁ ካለውዴታ በግዴታ የምትገለሉበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም። ማሽተት የማትፈልጉትን ነገር እንድታሸቱ የሚደረግበት ዕለት እየቀረበ ነው።

በቅድሚያ ግን ከዚህ በታች በፅሁፉ ለህዝብ ይፋ እንዲወጣና እንዲታወቅ የተደረገው ታሪካችሁ ታሪካችን አይደለም፣ እኛ የህዝብ ወገንና ከህዝብ ወግነን ስንታገል የኖርን ዜጐች ነን የምትሉ ካላችሁ ብዕራችሁን እንድታነሱና መልስ እንድትሰጡ እንጋብዛለን። በበኩላችን የምንናገረው እውነት፣ ብዕራችሁ የመከነ መሆኑን እናውቃለን። የምትታወቁት በሀሜታ በአሉባልታ፣ ስም በማጥፋትና ለጨቋኝ ገዢዎች አገልጋይ በመሆናችሁ፣ ለጥቅማ ጥቅም ብሎም ለፍርፋሪ ተገዢ በመሆናችሁ ብቻ ነው።

ሁላችሁም ተገቢውን የሀጢአትና የወንጀል ታሪካችሁን በአግባብ እንድትከናነቡ በቀንደኛዋ ፀረ ህዝብ በመሠረት መንግሥቱ (Dr ?) እንጀምር፥

፩. <u>መሠረት መንግሥቱ፡ የፍቅሩ ማሩ (ወያኔ እስር ቤት የሚገኝ) ባለቤት፡-</u>

በአገራችን አነጋገር “ባልና ሚስት ካንድ ውሃ ይቀዳል” የሚል አነጋገር አለ። ፍቅሩ ማሩና መሠረት መንግሥቱ የዚህ አባባል አይነተኛ መግለጫዎች ናቸው። የዚችን ግለሡብና የባለቤቷን ፀረ የኢትዮጵያዊነትና በአፍቅሮተ ነዋይ እየተገፉ የፈፀሙትን ወንጀልና በውጭ ነዋሪ የሆነውን ወገን ለመከፋፈል የተጫወቱትን አፍራሽ ተግባር ተንትኖ ለማቅረብ አንድ ፅሁፍ ሳይሆን፣ መድብለ መፃህፍት ያስፈልገዋል። ሁለቱም ሀኪሞች ነን ይላሉ፣ ሁለቱም የህክምና ሙያ ግድ የሚለውን ኢቲክስና ሞራል የማያሟሉ ስለሆነ በዚህ ፅሁፍ ያንን ቅፅል ተነፍገዋል። ለምን ብሎ መጠየቅ የሷና የሱ ፋንታ ነው። ፍቅሩ ማሩ የልብ በሽታ ልዩ አዋቂ ነኝ እያለ (ባይ ፓስ የቀዶ ጥገና) አደርጋለሁ በማለት ከፈረንጅ አገር የበሰበሰና ሊጣል የተዘጋጀን የልብ መለወጫ በኮንቴይነር በወያኔ ፍቃድ እያስገባ የስንት ዜጋ ህይወት እንዳጠፋ አገር ያወቀው ፀሀይ የሞቀው ጉዳይ ነው። ወያኔ መልሶ ጠፈረው። ወያኔ በዚህ የተካነ መሠሪ

ድርጅት ነው። መሠሪን መሠሪ በላው ይሏል ይህ ነው። ወያኔ ማኖ አስነክቶ የራሱን ጥቅም ሚሚላት ማን አህሎት!! ግማሹ እንዲከብር ይፈቅድለትና ቆየት ብሎ በካልቾ ይጥለዋል። ግሚሱን ዝፈን አመስግነን ይለውና ስግብግቡ ዘፋኝ የኪነትን ክብር አዋርዶ በአገኘው ገንዘብ ሲደሰት፣ ለቀም ያደርገውና ግብረ ሥጋ ያስፈፀመበትና በል ጥፋ ይለዋል። ውጭ አገር ሄደህ ትንፍሽ ካልክ ይህንን በግልፅ እናሰራጭብሃለን ይለዋል። ሰብዕናንም ታሪክንም አጣምሮ ማጣት ይላሉ ይህ ነው። መሠረት መንግስቱስ የማህፀን ክሊኒክ ከፍቼ ወገኖቼን እያከምኩ ነው የምትለው ሃቅ ነው?? ለማያውቅሽ ታጠኚ ማለቱ ጊዜው ነው። ከወያኔ ስውር ተልእኮ ተቀብሎ በዚህ መሰሉ ክሊኒክ ከ13 እስከ 28 ዓመት እድሜ ያላቸውን ወጣት ሴቶች የሚያመክን፣ ጭራሹኑ ለማህፀን በሽተኛነት መዳረግ ወገንን መርዳት ነው? ወደ ሳውዲ አረቢያ፣ የመን፣ አረብ ኢሚሬት፣ ካትር …ወዘተ ወያኔ ለግርድና የላካቸው ከ730 ያላነሱ ወጣት ሴት ልጆች በአንቺ ክሊንክ መካን ሆነው እንደቀሩ የማናውቅ መሰለሽ?

ወያኔ ከተባበሩት መንግስታት፣ ከአለም ባንክ፣ ከትላልቅ የውጭ ኮርፖሬሽን፣ ወዘተ ፋሚሊ ፕላኒንግ፣ ህዝብ ስለበዛ የውልደት ቁጥጥር በሚል ሳቢያ ከሚያገኘው በሚሊዮን ከሚቆጠር ገንዘብ በምክፈል፣ የማምከኑን ስራ አስፈፃሚዎች ከሆኑት አንዷ ሆነሽ እንደተንቀሳቀሽ በዚህም ሳቢያ ንብረት እንዳፈራሽ መች ስተነው! በተግባር ተመሳሳይሽ የሆነው ባለቤትሽ በእስር ቤት ገና መንፈቅ ሳይሞላው አንቺ በአሜሪካ ሬዲዮ ጣቢያና በወያኔ ቴሌቪዥን ጣቢያ እየቀረብሽ ለህዳሴ ግድብ አዎጡ ስትይን ወያኔ ሊያደርግሽ የሚችለውን ስለምታውቂ ሳይሆን ይቀርል? ወንድሞችሽን ጭምር በነፃ የማሰብና እድገታቸውን የማጎልበት መሰረታዊ መብታቸውን ጭምር ገፈሽ ለእርኩስና አፍራሽ አላማሽ አሰልፈሻቸዋል። ወገንን አርካሽ ወላጅን ጭምር አስወቃሽ መሆንሽ በተግባርሽና አጠቃላይ ጉዞሽ የበለጠ እየተረጋገጠ ነው። ብትናገሪና ብትሳደቢ ከህዝብ የወገኑትን፣ አንብቡ ብትይን ወያኔ በታጋይ ሃይሎችና በህዝብ ወገኖች ላይ በሱ ድጋፍና ማተሚያ ቤት የሚያፅፋቸውን ፀረ ወገን መጣጥፎች፣ አድምጡኝ ብትይን የቪኦዔ ገለፃሽን። ለነገሩ ቪኦዔ ላይ የሚጋብዙሽ በችሎታሽ ሳይሆን በግል ጓደኞችሽ በሆኑ ግለሰቦች ነው። በአጠቃላይ እዛም ዘለልሽ እዚህም ረገጥሽ ድምሩ ወያኔን ማገልገል ነው። የህዝብ ወገን የሆኑትማ አሜሪካ ወያኔን በመደገፍ በህዝባችንና በሃገራችን ላይ እየፈፀም ያለውን ግፍ በግልፅ ስለሚተቹ መቼ ለአሜሪካ ሬዲዮ ቃለ ምልልስስ ጓጉተው። ታሪክሽ የቆሸሸ፣ ጉዞሽ ሁሉ ከአልፋ እስከ ኦሜጋ ከገሞራው ታሪክና አላማ የተፃረረ፣ የመንግሥት ሰማያትንና የሚኦልን ያህል የተራራቀ ነው። ዛሬ ጊዜ ፈቀደና የገሞራውን አስከሬን ከነስራው ውጤት ለወያኔ አስረከብሽ። ይህም በራሱ ለወያኔ አገልጋይነትሽ ለመቀጠሉ እራሱን የቻለ ማስረጃ ነው።

2. <u>የሺ ወንድሜነህ፡ አንቺስ ማነሽ? እቺስ ማነች? ሕዝብ ይወቅ፣ ታሪክ ይፍረድ</u>

የሺ ወንድሜነህ በፈረንጅ አገር አኗኗርና የመበልፀጊያ መንገድ የገባት ብልጣ ብልጥ ሰው ነች። ቀደም ባሉት ዘመናት የኢትዮጵያን ሕዝብ ችግሮች ለመፍታት ህብረት አስፈላጊ ነው በተባለበት (አሁንም ህብረት አስፈላጊ ነው) ጊዜ ኢደህቅ በሚል የህብረት አካል ባልደረባ በመሆን ቢያንስ አንዴ ለኢድህቅ ስብሰባ አሜሪካ ሄዳለች። ጊዜ ሳይወስድባት ይህ ትግል ጊዜ ወሳጅና መስዋዕትነትንም ጠያቂ መሆኑን፣ ለዝናና ለጥቅምም ማገልገያ አለመሆኑን በመረዳት መስመሯን አጥፋ የዛሬ ህይወቷን ተያያዘች። ዛሬ ከወያኔ ጋር የማያጣላ ስውር ግልጋሎት እየሰጠች፣ በሌላው መሥመር ደራሲ የሚል ቅፅል ተላብሳ በፈረንጆች ድጋፍና ድርጐ መፅሃፍ እያሳተመች "የተደላደለ" ህይወት ተስፈዬ ከሚባል መኢሶን ባሏ ጋር እየኖረች ነው። ዛሬም የኃይሉን አስከሬን ለወያኔ ለማስረከብ ከተሰባሰቡ ፀረ ህዝቦች ጋር በመሆን

በሰብሳቢነት እያገለገለች ነው። በሌለኛው አኳያ በስዊድን የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ፀረ ወያኔ አቋም ያለው፣ በኢትዮጵያ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ እኩልነት ላይ የተመሠረተ አገራዊ ሉዓላዊነትን ጥያቄ ውስጥ የማያስገባ፣ ከጥበትና የዘር ፖለቲካ የጠራ አቋም ያለው፣ የኢትዮጵያውያን ማህበር በስዊድን ለማቋቋም ያላቸውን ፍላጐት በግልፅ እየተናገሩ ሳለ፣ እሷና መሰሎቿ የወያኔ ጀሌዎችና ስላቶች ባልተገለሉበት የኢትዮጵያ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ እኩልነት ትርጉም የለሽ በሚሆንበት መንገድ የኢትዮጵያ ማህበር የሚባል እንዲቋቋም ቀን ከሌሊት እየጣረችእየጣሩ ናቸው። በዚህ ውስጥ ያሉ ግለሰቦች እሷን ጨምሮ ዝቅ ብሎ ታሪካቸው ይገለፃል። የተቀሩት ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር የወገኑ የጠራ ፀረ ወያኔ አቋም ያላቸው ዜጐች ሁኔታውን በቅድሚያ ስላጤኑ በስውር እየተገናኙ ጠንካራ ከህዝባችን ጋር የወገነ ፀረ ወያኔ የኢትዮጵያ ማህበር ለማቋቋም ጉዛአቸውን ጀምረዋል። የዚህም መሆን ሁለገብ ትግሉን ያጠራል። የነሱን ወያኔያዊ ተልዕኮ ይበልጥ ያጋልጣል። የሺ! ተሸፋፍኖ ጉዞ ዘመኑ አብቅቷል። እነገሞራው በኖሩበት በተሰቃዩበት አገር አንቺ ደራሲ እየተባልሽ የደራሲ ድርጐ እየተቀበልሽ መኖርሽ እራሱ የሚገልፀው ብዙ ነገር አለው። አንቺ ለመሸፋፈን ብትሞክሪ የማይሸፈነው ታሪክሽ ይከተልሻል። የፅንሰ ሃሳብም ሆነ የንድፈ ቃል የማይሰፍርበት፣ ስለኢትዮጵያ ሕዝብ ስቃይና እሮሮ የማይነሳበት ፅሁፍሽ በፈረንጆች የሚያሸልምሽ፣ ግን እነ ኃይሉ ገሞራውን የሚያሰቃይ መሆኑም፣ በቀጣይነት የረከሰ ታሪክሽ አካል ሆኖ የሚቀር ነው። አንቺና መሰሎችሽ ቆማችሁ ከነታሪካችሁ ሞታችኋል። እነኃይሉ ግን ሞተውም በታሪካቸውና በተግባራቸው ዛሬም ሆነ ወደፊት ህያዋን ናቸው።

3· <u>አብርሃም አገኘሁ፡-</u>

ይህ ዋልጌ! ኤርትራዊና ወሎ ያደገ ቀደምት የመኢሶን አባል፣ ዛሬ ደግሞ የወያኔ ሰላይና ግንባር ቀደም አገልጋዮች ሆነው ከሚፈረጁት አንዱ ነው። ይህ ግለሰብ በፖለቲካ ንቃቱና በአጠቃላይ ሁኔታዎች ግንዛቤውም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያለ መሆኑ ግልፅ ቢሆንም፣ እያደረሰ ካለው ጥፋት አንፃር ልዩ ትኩረት ሊደረግበት የሚገባ አጥፊ ሰው ነው። ቅዳሜ ማታ የገሞራው አስክሬን ለወያኔ በገፀ በረከትነት ከተላከ በኋላ ሰው እንዲሰባሰብ የተደረገው ይህ ከንቱ ግለሰብ "ልጁን ይሁን እህቱን" ከዛሬ ሁለት ወር በፊት ሲድር ወያኔዎች በነቂስ ወጥተው ውስኪ ሲራጩበት ከነበረ አዳራሽ ነው። የዚህ መሆን በራሱ እጅግ የሚያስቆጭ ትግላችንን የበለጠ እንድናሰባስብ መልዕክት ሰጪ ነው። ይህን ግለሰብም ሆነ ከወያኔ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን ሁሉ በማህበራዊ ህይወታቸው ጭምር ማስገለል እንጂ እነሱ ውስኪ የሚራጩበት ቦታ መገኘት በራሱ አሳፈሪ ነው። ዘረኞችንና አገር አጥፊዎችን አጥብቆ መጥላት እንጂ፣ እየጠሉም መውደድ በትግል ቋንቋ ቦታ የለውም።

4· <u>ሙሉጌታ ጥበቡ፡-</u>

ይህ ግለሰብ በሚገባ መታወቅ ያለበት በገሞራው አስክሬን መላክም ላይ በአገር ቤት ሁሉን ነገር ያቀናጀና፣ ገሞራውም በህይወት እያለ የወንድሙ ልጆች ወደ ገሞራው የሚልኩትን ደብዳቤዎች በራሱ አድራሻ አድርጐ ለገሞራው የሚያመላልስ ማሽንክ ሰው ነው። በተቻለው መንገድ ግን እራሱን ደብቆ የሚኖር፣ ሰው በብዛት በተሰባሰበበት ሀገራዊና ወገንተኝነትን ማሳየት ግድ በሚሉ ስብሰባዎች ላይ ሁሉ የማይገኝ መሠሪ ፍጡር ነው። ገሞራው! የሚያመጡለትን ደብዳቤዎች ሁሉ ቀድምት፣ የወንድሞቹ ልጆች በተለይ ቆንጂት የምትባልው አስክሬኑን ለማጅብ መጥታ መሠረት መንግሥቱ ቤት መሽጋ ያለችው ባቀረሉበት ጥያቄ እጅግ በጣም፣ ስላዘነ ደብዳቤዎቹን ከፍቷቸው ወይም አንብቧቸው አያውቅም። ይህ ግለሰብ ከወንድሙ ጋር ባለ አራት ፎቅ ህንፃ እያሰራ ለሁለት ወር አዲስ አበባ ከርሞ፣

ገሞራው ማረፉ በተሰማ በሦሥተኛው ቀን ቆይታውን አሳጥሮ፣ ተንኮሉና መሠሪነቱን እንደተላበሰ ወደ ስዊድን ተመለሰ። ይህ ግለሰብ አንድም ጊዜ በህይወቱ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ወግኖ የቆመበት ታሪክ ጭራሽ የለውም። አለኝ የሚል ከሆነ ብዕሩን ያንሳ። ሰው አነስ ካለለትና አቋማቸውን ካጠና በኋላ ግን ጥቁር አንበሳ ሲሰራ፣ የቀበሌ ታጣቂዎችና፣ የደርግ አረመኔ ገዳዮች ሊይዟቸው ካልቻሉም ሊገሉአቸው ሲመጡ፣ ቆራጥ የህዝብ ልጆችና የህክምና ተማሪዎች፣ ሞት ለፋሽሽቶች ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ እያሉ ሳይናድ ታብሌታቸውን እየዋጡ እንደሞቱ ይመሰክርል። አንዳንዴም ታሪካቸውን የራሱ ታሪክም ለማድግ ጥረት ሊያደርግ ሲሞክር ይታይበታል። ዛሬ ግን ጡረታውን በፈረንጅ አገር አስከብሮ፣ "ወያኔ ለባለሀብት" ተሰጥቷል የሚለውን "መብቱን" ለማስጠበቅ ለወያኔ ሙሉ ለሙሉ እጁን ሰጥቷል። ከሁለት ወር ቆይታው ከተመለሰም በኋላ በተለይም የእኋለ ልጆች ገሞራው እዚህ ይቀበር የሚል አቋማቸውን እንዲለውጡ ሊያደርግ የሚችለውን ሁሉ አድርጓል። ይህ ብቻም አይደለም፣ ገሞራው ከወንድሞቹ ልጆች የተቆራረጠበት ዋነኛ ምክንያት እንዴት ወያኔ ኤንባሲ ሄጄ ወራሽነቴን አረጋግጬ ለነሱ እንድሰጥ ይጠይቁኛል የሚለው ጉዳይ ነበር። ገሞራው ይህንን ጉዳይ ሳይቀበልም እንዴት ወያኔ የሱን ድርሻ ጭምር እንዲሸጡ ፈቀደላቸው ሲባልም፣ ይህ መሠሪ ግለሰብና የራሱ ወንድም እንዲሁ ሌላ ሶስት ሰዎች በወያኔ በኩል አስፈፃሚ መሆናቸው ሊረጋገጥ ችሏል። ይህን ሁሉ ደባና ተንኮሉን እንደያዘ የሚያሳንፀውን ህንፃ እሱ ይኑርበት አሊያም ትግሉ ይቅደመው ለጊዜ ሰጥተን የምናየው ይሆናል። እስከዚያች ዕለት ሃላፊነታችን የኢትዮጵያ ሰፊ ህዝብ ጠላቶቹን እንዲያውቅ ታሪካቸውን ባልተዛባ መንገድ ማስቀመጥና የኢትዮጵያ ህዝብ እንዲያውቃቸው ማድረግ ነው።

5. ክፍሌ ጆቴ፡-

ሶቭየት ህብረት ሳለ ኢሕአፓን የሚደግፍ የተማሪዎች ማህበር አባል ነበር። ስዊድን ሲገባ ካገር ቤት ባስመጣት ባለቤቱ ተገዶ ሰው በተሰበሰበበት በራሱ ቤት እየቧጨረችውና እየቧጠጠችው አነግ እንዲሆን የተገደደ፣ የፀና አቋምና ቆራጥነት የጐደለው ግለሰብ ነው። ሰንበት ብሎም አንድ እግሩን ከኦነግ ሳይነቅል በሌላ እግሩ ደግሞ የመራራ ጉዲና ድርጅት አባልና በዚህ አገር ተጠሪ ሆኖ እየሰራ ያለ ሰው ነው። አሁን ደግሞ የገሞራውን አስክሬን ለወያኔ ገፀ በረከት ለማድረግ ከሚሰሩት የለየላቸው ፀረ ህዝቦች ጋር ተባበሪ እየሆነ ያለ ነው።

6. ስዩም አዲስስ ማነው?

FEODOR DOSTOEVESKY ራሺያዊው የስነፅሁፍ ሰው "ምክንያቱን አግባብ ባለው መንገድ መግለፅ ቢከብድም አንዳንድ ጊዜ እርኩሳን መናፍስት በቅዱስን ቤት ያድራሉ" ይላል። አቶ አዲስ አለማየሁ በጠቅላላው የኢትዮጵያ ሕዝብም ሆነ በታጋይ የህዝብ ልጆች በጣም የተከበሩና የተወደዱ የነበሩና ዛሬም በስራቸው የተመሰገኑ ናቸው። መፃህፍታቸው በሞላ እውነትን የተላበሱ፣ ጣዕምና ውበት በተሞላበት መንገድ በተላያዩ ስርዓቶች ውስጥ የኢትዮጵያን ጭቁን ህዝብ ብሶት የገለፁበት ክንውኖች ናቸው። ዘር፣ ጐሣ፣ ነገድን አካለው የገለፁት ስንኝም ሆነ ሀረግ በሥራዎቻቸው ውስጥ ጭራሽ አልታዩም። ዛሬም በሕይወት ቢኖሩ አማራው ሲፈጅ አማራ፣ ኦሮሞ ሲጠቃ ኦሮሞ፣ አፋሩ ሲመታ አፋር እሆናለሁ የሚል አቋም ይይዛሉ ብለን አናምንም። ሊይዙ ይችላሉ የሚል ከሆነ ልጃቸው ስዩም መልስ ይስጥበት!! የኢትዮጵያ ህዝብ ተባብረህ ይህንን ጥቃት መክት የሀገርህን ህልውናና መብትህን አስከብር ሊሉ እንደሚችሉ ግን ጥርጣሬ የለንም።

ታዲያ! ስዩም አዲስ፣ ወያኔ በቀደደው ቦይ ፈሶ ሞረሽ ሞረሽ ማለትን ከየት ተማረው?። በርግጥ አቶ አዲስ አለማየሁ በሥጋ የወለዱዋቸው ልጆች ባይኖራቸውም ስዩምን የእህታቸውን ልጅ ተቀብለውና ተንከባክበው ያሳደጉት በራሳቸው ቤት ነው። ይህን ከመሠሉ ታላቅ ኢትዮጵያዊ ቤት መገኘት የነበረበት ትምህርት ይህ ነው? ወይስ ዶስኮቪስኪ ያለው እርግጥ ነው ብሎ ማለፉ ይሻላል!!

የተከበሩ የሀዲስ አለማየሁ ወራሽ መሆን ሌላ፣ ስራቸውን ማስተዋወቅና ማስረዳት ድግሞ ለየቅል ናቸው። ስራቸውን ማስተዋወቅና ማስረዳት በሞያው የተሰማራ መሆንን፣ በአቋምና በአመለካከትም መቀራረብን ይጠይቃል። ሥራና ሙያ በዘፈቀደ የሚወረስ አይደለም። የሥራቸውን ውጤት የመውረስን መብት ማስጠበቅ ደግሞ ሌላ ነው። ካለሙያና ችሎታ የእሳቸውን ስራዎች ለማስረዳት በእስራኤልም መዞር ግን ሥራቸውን ጭምር ማርከስና ማዛባት ይሆናል። የነዚህን ሁኔታዎች ግንኙነትና ልዩነት ካለመገንዘብ ይሆን አቶ ስዩም የታላቁን ኢትዮጵያዊ የስነፅሁፍና የፍልስፍና ሊቅ የኃይሉ ገሞራውን እስክሬን ለወያኔ ለማስረከብና ስራዎቹንም በገፀ በረከትነት ለማቅረብ በሚደረገው የዘረፋ እቅድ ውስጥ ገብተው የተዘፈቁት???። መልስ ከራስዎ! ለሚከተለው ጦስ ውርድ ከኛ ብለን ለጊዜው እንዝጋው።

7· ኤልያስ ሥዩም (እውነተኛ ስሙ ሽምሱ) እና ሰለሞን ተድላ (ባለምግብ ቤት)

እነዚህ ሁለት ግለሰቦች ከወያኔ ዘረኛ ቡድን ጋር ከፍተኛ የንግድ ትሥሥር ያላቸው ፀረ ሕዝብ ግለሰቦች ናቸው። ኤልያስ ሥዩም ከአዲስ አበባ ዘፈኞች እያስመጣ ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ እያካበተ ያለ ነው። ከወያኔ በተሰጠውም የጐን ሥራ በመመርኮዝ የፀና ፀረ ወያኔ አቋም ያላቸውን ኢትዮጵያውያን ሥም እየሰበሰበ በቀንደኛው ወያኔ በክንፈ ሃጐስ በኩል ለወያኔ ኤንባሲ የሚያቀብል ሰው ነው። ሰለሞን ተድላ ከወያኔ ሰዎች ጋር የከረመ ግንኙነት የፈጠረ ስለሆነ በስዊድን የሚሰራጨውን የእንጀራ፣ የመጠጥ፣ የበርበሬና ቅመማ ቅመም በሞኖፖል እንዲይዝ ከወያኔ ገፀ በረከት (ገፀ እርግማን) የተሰጠው ነው። እነ ነዋይ ደበበን የመሰሉ ፀረ ህዝብ ዘፋኞች ሲመጡም ልምምዳቸውን የሚያደርጉት በሱ ሆቴል አዳራሽ ውስጥ ነው። ሁለቱም ከወያኔ ኤንባሲ የማይጠፉ፣ ግልፅና ሥውር ትዕዛዝ ከወያኔ በመቀበል ያሚያገለግሉት ናቸው። ዛሬም የኃይሉ ገ/ዮሐንስን እስክሬን ለወያኔ ለመሸጥ ርብርብ እያደረጉ ካሉት ግለሰቦች (ከላይ የተዘረዘሩት) ጋር ግንኙነት በመፍጠር የጀርባ ድጋፍ እየሰጡ ያሉ ግለሰቦች ናቸው። በስዊድን የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የወያኔን ኢኮኖሚያዊ አቅም ለማዳከም ይረዳ ዘንድ፣ ሀ) በወያኔ አየር መንገድ መጓጓዝ ውግዝ እንዲሁን፣ ከህዝብ አፍ እየተነጠቀ የወያኔን ኢኮኖሚ በሚያዳብሩ ቁሳቁሶች በአጠቃላይ እቀባ እንዲደረግ ጥሪ ሲያደርጉ እነ ሰለሞን ተድላ በወያኔ ጉያ ተወሽቀው እቅዱ ተግባራዊ እንዳይሆን የሚንቀሳቀሱ ናቸው።

8· ሢራጅ ዴታንጐ እና ኃይለማርያም ደንቡ

እነዚህ ሁለት ግለሠቦች ገሞራው በሕይወት እያለ፣ ታሞ በነበረበትና ተሽሎትም ከተነሳ በኋላ ከፍተኛውን ሤራና ግፍ የፈፀሙበት ናቸው። ኃይሉ እስከምናውቀው ድረስ የአዕምሮ በሽተኛም ሆኖም ወይም ዝርዝር ነገሮች የመርሳት (ዲሜንስ) ተይዞ የሚናገረውንም ሆነ የሚሰራውን በጭራሽ ስቶ አያውቅም። እነዚህ ሁለት ግለሰቦች ግን ሁሉን ነገር ያምታታል፣ ቀኝና ግራ እጁንም አይለይም ...ወዘተ እያሉ ገሞራው ለሚኖርበት COUNTY (ቀበሌ) ሃላፊዎች ስላስታወቁ፣ የቀበሌው ኃላፊዎችም ይህንኑ ስለተቀበሉ ለገሞራው በየወሩ ለመኖሪያው፣ ለቤት ኪራይ የምትሰጠው አነስተኛ ገንዘብ በዕጁ

እንዳይሰጠው አስደርገዋል። እንደ አእምሮ በሽተኛና ዕብድ አስቆጥረውት ለሱ እንድ ምስለኔ ተወክሎ የቤት ክራዩን የሚከፍል፣ ለመብራትም ሆነ ለትናንሽ ወጪዎች ሁሉ ሃላፊነት ተቀብሎ የሚከፍል የካውንቲ ሠራተኛ ሰው አስመድበውበታል። ይህ ታላቅ ኢትዮጵያዊ ፈላስፋና የጀግና ጀግና እህል አምሮት፣ ሻይ ፈልጎ ወጣ ልበል ቢል እንኳ በተጣለበት የግፍ ውሳኔ በኪሱ ገንዘብ የለውም። ኃይሉ ገሞራው እነዚህ መሠረታዊ ፍላጎቶቹ እንዳይጓደሉበት ግን፣ የሱን ትልቅነትና ለአገራችን ቅርፅ መሆኑን የተገነዘቡ የህዝብ ልጆች፣ ከወር ገቢያቸው ላይ በየወሩ በመክፈል እነዚህ ሁኔታዎች እንዲሟሉ አድርገዋል። ዛሬ እሱ በህይወት በሌለበት ሁኔታ ዝርዝሩን ማንሳት አንፈልግም። ዛሬ ጐሞራው አልፎም ለሱ ያለን ክብርና ፍቅር እንዳለ ነው። ከላይ የተጠቀሱት ሁለት ግለሰቦች ይህም ብቻ ይበቃዎል አላሉም። ዳግም ከፈረንጅ ባለስልጣኖችና ሃላፊዎች ተመሳጥረው፣ ቤቱ ሊኖር አይችልም የሚል ውሣኔ እንዲደረስ አድርገው፣ የአእምሮ እክል ያለባቸው በዲሜንስ በሽታ በተያዙ ሽማግሌዎች ወደ ሚኖሩበት ከቤቱ በጣም ወደራቀ ሰፈር እምቢ እያለ እንዲወስድ ተደረገ። ያስገቡት ሠፈር ከላይ የተጠቀሰው ሢራጅ ዴታንጐ ሰፈር አካባቢ ነው። እዛም እያለ እየሄድን እንጠይቀው ስለነበር ብሶቱንና ምሬቱን ያስረዳን ነበር። እኛም የተወጋው ውግ ከአቅማችን በላይ መሆኑን ብናውቅም፣ በርታ አትበሳጭ ይሄም ያልፋል ማለታችንን አላቋረጥንም። ያለበትን ሁኔታ በሞላ ከዚህ አገር ውጭ ላሉ የእምነት ወገኖቹ በጊዜው ስላስታወቅን፣ በአጣዳፊ ኃይሉ ገብረዩሀንስ ከዛ ቦታ ወጥቶ ወደቤቱ እንዲመለስ የሚል ትዕዛዝ ስላተላለፈ፣ ኃይሉ እንደፈለገው ቤቱ ውስጥ አረፈ። ኃይሉ ሞትን ጭምር የማይፈራ የፀና እምነት ባለቤት ነው። እስር ቤቶችንማ ያውቃቸዋል። ቤቱ ከገባ ቆየት የት ብሎ ልንጠይቀው ስንሄድ ያስገቡህ ቦታ ኑሮ እንዴት ነበር ስንለው፣ "<u>ያችን ትንሿን እስር ቤት ነው የምትለኝ? እሷ እኮ ቀላል ነች! የዕስሩን ጉዳይ እንዳልረሳው ሊያስታውሱኝ ነው ከቤቴ የወሰዱኝ!" ይለን ነበር፣ እየቀለደ።</u>

ኃይለ ማርያም ደንቡ የራሱን አስፀያፊ፣ አስነዋሪና አሳፋሪ ታሪክ በጀርባው ተሸክሞ፣ ከዚህም ሳይፀዳ ለዘረኛው ወያኔ እጁን የሰጠ ግለሰብ ነው። መሠረቱ መኢሶን ነው። እንደታሪክ ተጐዳኞቹ ከገቡበት አዘቅት መውጫው ተስኖት ጥቅም ፍለጋ ከወያኔ ጉያ ተሸጉጦ እየኖረ ያለ ነው። በፋሽሽቱ የኮረኔሉ መንግሥቱ ዘመን ወደ ሶቭየት ህብረት ተልዕኮ ከኤንባሲው ጋር እጅና ጓንቲ በመሆን ለመሠረታዊ ለውጥ ይታገሉ የነበሩትን የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎች የስም ዝርዝር ለኤንባሲው እያቀረበ በግዴታ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለሱ ያስደርግም ነበር። ይህ ተግባሩን በዛ ጊዜ ሶቭየት የተማሩና በህይወት ያሉ የህዝብ ወገኖች የሚመሰክሩት ጉዳይ ነው። በግዴታ ከተላኩት ገሚሶቹ በእስር ከማቀቁ በኋላ ሲገደሉ፣ ገሚሶቹ እስከዛሬም በሕይወት አሉ። በአንድ በኩል ያነበብኩ የነደድኩ ማርክሲስት ነኝ ይላል። እሱና ማርኪዝም ግን በተግባር የተቃረኑ ናቸው። ስለማርኪዝም ሌኒኒዝም ሲያወራ ጨርሶ ያነበበው ሥራቸው አለወይ ያሰኛል። የኖረበት አገር የሶቭየቱ ሌኒን የዚህን መሠል ሰዎች "ግማሽ ጥብስ አብዩተኞች ይላቸው ነበር"። ይህ ማርክሲስት ነኝ የሚለን ኃይለማርያም ደነቡ ንብ እርባታ ከፍቶ ለወያኔ እጁን ሰጠ። ወያኔ! ለራሱ እንጂ ለብልጣ ብልጦችስ መች ተመቸ!!። የንብ እርባታውም ውጤታማ አልሆነለትም። በህዝብ የመጠላት ደረጃውን ግን አሳደገ!! እሱንም ሢራጅ ዴታንጐንም ሕዝብ ይወቃቸው!! ኃይሉ ገሞራው ላይ ያካሄዱት ሤራና የፈፀሙት በደል ቀን ይጠብቃል እንጂ ማስጠየቁ አጠያያቂ አይደለም።

ከሦሥት የማይበልጡ ፀረ ሕዝቦችና የወያኔ ዓላማ ሥውር አገልጋዮችን ታሪክ ይፋ ማድረግ ይቀረናል። የነዚህንም ፀረ የኢትዮጵያ ህዝብ እንቅስቃሴና መሠረታዊ ታሪካቸውን በቀጣዩ ፅሁፋችን እናቀርባለን። እንደ ጃርት ከተደበቁበት ጉድጓድ አውጥተን ከህዝባችን እናስተዋውቃቸዋለን።

ለጊዜው ግን ታላቁ የሥነፅሁፍና የፍልስፍና ሊቅ ጋይሉ ገብረዮሐንስ ካረፈ በኋላ የታዘብነውን በማንሳት እንደመድማለን። የገረመን ትልቅ ነገር ጋይሉን አላውቀውም የሚል ሰው መጥፋቱ ነው። ወጣቶቹ አበው ሽማግሌዎችና እናቶች፣ የወያኔ መልዕክተኞችና ሰላዮች፣ በገሞራው የኑሮ ሁኔታ ተሳላቂዎች፣ በተቃውሞ ሠልፍ ላይ ጋይሉን ዘላፊዎችንና አንጓጣጮች፣ ከታሪክ ከርሰ መቃብር መውጣት የተሳናቸው መኢሶኖች ...ወዘተ ሁሉ ጋይሉን እናውቀዋለን ባይ መሆናቸው ነው። ጋይሉን የሚያውቀው ዕድሜ ልኩን ፍዳና ስቃይ ለሱ ሲል የተቀበለለት ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብና የሱን አላማና ፅናት ተጐናፅፈው፣ ለሱ አላማ ቆመው ከህዝብ ወግነው እየታገሉ ያሉት ብቻ ናቸው። የተቀረው በሞላ ጋይሉን ጭራሽ አያውቀውም። ማወቅና ዓላማ እጅጉን የተሳሰሩ ናቸው።

በርግጥ ጋይሉ ሁሉንም ያውቃል። የጋይሉ ፍልስፍናና የስራዎቹ ሁሉ መሠረት ሰብዓዊነቱ ነው። ጋይሉ ሰብዓዊ ክብርና ትሕትና የሚሰጠው ኢትዮጵያ ውስጥ ለተፈጠረው ሠው ብቻ አልነበረም። በዓለም ዙሪያ ፍዳና መከራ እየተቀበለ ላለው ሁሉ ነው። ሲጨነቅ ሲጠበብ የኖረውም ለዚህ ነው። ህፃን፣ ወጣትና ሽማግሌ፣ ሴትና ወንድ ሳይለይ በሰብዓዊነታቸው ያከብራቸዋል። በዚሁ ልክ በተለያየ መንገድ ይህን ሰብዓዊ ፍጡር የሚያሰቃዩትን አምርሮ ያወግዛቸዋል፣ ከልቡም ይጠላቸዋል። ስለዚህም ነው በረከተ መርገምን ሲፅፍ ሰው በሚለው ጀምሮ ሰው በሚለው የሚደመድመው።

በትክክለኛ ቋንቋ ጋይሉን አውቀዋለሁ ማለት የሚቻለው እሱ የቆመላቸውን እምነቶቹን መከተል፣ በየዕለት ኑሮአችንም እነሱን ለመተግበር መታገል ማለት ነው። ማወቅና እውቀት ፍቺ ያጡበት ዘመን ላይ መድረሳችን በራሱ እግዚዖ የሚያሰኝ ነው። የጋይሉ ጥምር ሥራ ማዕከላዊ መልክት፣ በዚህ መሰሉ የአጭበርባሪዎች ትውውቅና ዕውቀት፣ ጭቆናና ግፍ ላይ የተመሠረተ ዓለም ይለወጥ፣ የብዙሃን ንብረት ይሁን ነው መልዕክቱ። ለእኛም ጋይሉን ማወቅ እምነቱና አላማውን ተከትለን ኢትዮጵያና ሕዝቧን የሚጎዱትን ሁሉ መታገል ነው። በዚህ መስመር ስለምንጓዝ ዛሬም ጋይሉ ለኛ ህያው ነው!!!